# <u>መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል</u>

ወያኔን በሚመለከት መስረቅ የለመደ ከእናቱም ይሰርቃል ማለትም ያስኬዳል፡፡ የወያኔ ቡድን መስራቾች-- ይህ የዚያን ጊዜ ካድሬውን መለስን አይመለከትም-- ገና ጎህ ሳይቀድ የትግራይ መሬት ከሱዳን ይዋሰናል ብለው የጎንደርን ለም ክፍሎች ወደ ትግራይ ጠቅልለውና ከወሎም እንዲሁ ቦጭቀው የትግራይን ካርታ አስፍተው ስለው ነበር፡፡ ከመለስ ተጣላን የሚሉት የወያኔ የቀድሞ መሪዎች ዛሬ የወልቃይት ጠገዴ ና ሌሎች ወደ ትግራይ የተሰረቁ መሬቶች ጉዳይ ሲነሳ ወልቃይት ጠገዴ ሕዝበ ውሳኔ ያካሂድ ብለው ሲያላግጡ ተደምጠዋል፡፡ የጎንደርና የወሎን መሬት ማለትም የእናት ኢትዮጵያን መሬት ሊሰርቅ የተነሳው የወያኔ ቡድን የሀገርን መሬት ለባዕዳን ማስማማቱና መሸጡ በእውነቱ ሊያስገርም የሚገባ አይደለም፡፡

ዛሬ የወያኔ ቡድም ለሱዳን የሀገራችንን መሬት ሸጧል፡፡ ለሳወዲ አረብያ ደግሞ ሰፊ ለም መሬት አለና ልስጣቸሁ ክፈሉኝ ብሎ እየተለማማጠ ነው፡፡ በአባይ ሸለቆና ሌሎች ቦታዎች ማዕድን ፈልጉ የተባሉት እነ  ፋልከን ኩባንያ የኤሚራት አረብ ኩባንያ ናቸው፡፡ በእናቱ ኢትዮጵያዊ ግን ዜግነቱ ሳውዲ የሆነ ግለሰብ ቱጃርም ሀገር ተለቆለት በኤኮኖሚ ላይ ጤነኛ ያልሆነ ቁጥጥር ማስፋፋት ብቻ ሳይሆን ሕዝብን ንቆም በይፋ ለገዢው ቡድን ፖለቲካዊና የገንዘብ ድጋፍ እየሰጠም ነው፡፡ በቀጥታና በእጅ አዙርም የአረብ ሀገሮችና ከበርቴዎች  የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ላይ ጎጂ ቁጥጥር ይኖራቸው ዘንድ የመለስ ቡድን አመቻችቶላቸዋል፡፡ ቻይና የተሰጣት ስልጣን ሰራተኛ እስከ መደብድብ ድረስ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ የወያኔ ባለስልጣኖች ከህንዱም ከቻይናውም በቂ ጉቦ እየበሉ ለሀገራችን መንገድ የማይሆኑ አውቶቡሶችና መኪናዎችን ሲያስገቡ፣ የማያዋጣ ኮንትራት ሲፈራረሙ ወዘተ ታዝበናል፡፡ የወያኔ መሪዎችንና ድርጅቱን በቅርብ ከሚያውቁት የሻዕቢያ መሪዎች አንዱ የሆነው በቅርቡ በሰጠው ቃለ መጠይቅ የወያኔ መሪዎችን ከበግ አመሳስ ሏቸዋል፡፡ በደግነት ወይም የዋህነት ሳይሆን ሳራቸውን ካገኙ--ገንዘባቸውን ካስገቡ-- ለሌላ ግድ እንደሌላቸው ለመጠቆም ነው፡፡ በሀገራችን መሬት የባዕድ ሀገር ወታደሮች ሰፍረው እንደልባቸው በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ይከበራል፣በመሬቷ ማንም የባዕድ ጦር አይሰፍ ርም፣ የጦር ሰፈር አያቋቅምም የሚለውን መሰረታዊ አቅዋም የወያኔ ቡድን ተፃሮ ይገኛል፡፡ ሀገርን ሸጧል፡፡

የወያኔ ድርጅት ይህን የመሰለና ቅልጥ ያለ ፀረ ኢትዮጵያነት ያንፀባረቀውና እያንፀባረቀ ያለው በድንገት ወይም በአጋጣሚ ሳይሆን ከስረ መሰረቱ ከሀዲ በመሆኑ ነው፡፡ በስድሳዎቹ መጀመሪያ የኢትዮጵያ ተራማጅ ወጣቶች በዴሞክራሲያዊ ትግል ዙሪያ በኢትዮጵያዊነት ሲታገሉና ሲደራጁ የተወሰኑ ጠባበ. ብሄረተኞችና ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ግን በብሄረሰብ ደረጃ ውስጥ ለውስጥ መደራጀት ጀመሩ፡፡ ህብር ብሄር በሆነው የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ሳይሆን

በራሳቸው ጠባብ ቡድን ተደራጁ:: በኢትዮጵያዊነት የሚታገሉትን የትግራይ ተወላጆችን ደግሞ የሸዋ ኮራኩር፣ የአማራ ሎሌ ብለው መዝለፍንም ተያያዙት:: የኤርትራ ግንባሮችም ለራሳቸው ግብ ሲሉ እነዚህን ጠባብ ቡድኖች ደግፈዋል፣አበረታተዋል:: ይህ ጠባብ ስብስብ ከውልደቱ ኢትዮጵያን በጥላቻ እያየ ፣አማራ ያለውን ሕዝብ በጠላትነት እያወገዘ ለጥፋት የተፈጠረ ነበርና በዚሁ በጠመመ ይዞታው ባጅቶ ዛሬ ከየትም ቢሆን አፍቅሮ ኢትዮጵያን ሊወልድ የሚችል አይደ ለም:: በ1967 መርህ ግብር ወይም ጦማር/ማኒፌስቶ ብሎ ሲያወጣም የኢትዮጵያ ሕዝብ በብሄረ ሰብ ደረጃ ተከፋፍሎ እርስ በርስ የሚባላ ነውና ሁሉም ተገንጣጥሎ የየራሱን ነፃ ሬፑብሊክ ያቋቅ ም ብሎ ተፈጥሞ ነበር:: መለስ ዜናዊ ፀረ ኢትዮጵያነትን የወረሰ ሊሆን ቢችልም እንደ ቡድን ወያኔ ዘረኛና ጠባብ በመሆኑ ስብህት ነጋ ተባለ ሌላ ሁሉም የወያኔ ቁንጮዎች ኢትዮጵያን ይጠላሉ:: መለያችን ትግሬነታችን ነው ሲሉም ከዚህ ሌላ ለአሳር ማለታቸው መሆኑን የሚስት የለም:: በመሆኑም እስካተረፋቸው ድረስ የማይቸበችቡት የኢትዮጵያ መሬትና ክብር የለም ብንል ማጋነን አይሆንም:: ከአልጄረሱ ስምምነት ካሉት. በኋላና የዓለም ፍረድ ቤት አዱ ኢሮብና ሌላም መሬትን ለኤርትራ ሲሰጥ ድል ብለው ሊያወናብዱ ሞክረውም እንድነበር የሚታወስ ነው: : ወያኔ የራሴ የሚለውን ትግራይ ከሌላው ቢያስቀድምም ካዋጣው ትግራይንም ለመሸጥ ዓይኑን የሚያሽ ቡድን አይደለም:: ለዚህም ነው የመለስ ዜናዊ ቡድን ክህደት ቀጣይ እንጂ ቢዘህ የሚገ ታ የማይሆነው::

በአባይ ወንዝ አጠቃቀም ላይም ቢሆን የመለስ ቡድን የኢትዮጵያን ጥቅም አላስጠበቀም:: መለስ ዜናዊ አረብ ነኝ፣ ኢትዮጵያም ወደ አረብ ራቢጣ ትገባለች ብሎ ለሊቢያው መሪ ለገዳፌ መዋሸቱ በቪዲዮ ተቀርፆ ያለ መረጃ ነው:: ወያኔ በጫካ ሳለ ሱዳን ያዘዘውን ሁሉ ሲያስፈፅም፣ ደቡብ ሱዳኖችን ሲያስገድል፣ደን ሲያስጨፈጭፍ እንደነበር የሚታወቅ ነው:: ባዕዳን የጠየቁትን ሁሉ እያሟላና ኢትዮጵያን እየጎዳ ለስልጣን ደርሷል:: ስልጣን ሲይዝም ኢራንና ሱዳን አክራሪ ተልዕኮ አቸውን እንዲወጡ፣በሀይማኖት ስም ባዕዳን ሀገርን እንዲጎዱ በር መክፈቱ የሚታወስ ነው:: ይህ ሁሉ እያደረ ቀጥሎና ተባብሶ ነው ዛሬ ደግሞ መሬት ቆርሶ መስጠት የተጀመረው:: ተጀመረ እንጂ አላበቃም ብንል ትክክል ነው:: የመለስ ቡድን በስልጣን እስከቆየ ድረስ የኢትዮጵያ መሬት ና ክብር ለገበያ መቅረቡ ቀጣይ ክስተት ይሆናል:: ለዚህም ነው ትግላችን ተፋፍሞና ተጠናክሮ የመለስን አገዛዝ ደምስሶ ኢትዮጵያን ከጥፋት ማዳን ያለብን::